## የቃላት ጥያቄዎች

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ምድቦች ውስጥ የስፋት መለኪያ ምድብ ያልሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) ሜትር ካሬ　　ለ) ሚሊ ሊትር ካሬ

   ሐ) ሄክታር　　መ) ሳንቲ ሜትር ካሬ

2. የአንድ ካሬ የጎን ርዝመት 6 ሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል?

   ሀ) 48　　ለ) 36

   ሐ) 24　　መ) መልስ የለም

3. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠለል ምስል ርዝመቱ 10 ሳ.ሜ እና ወርዱ 8 ሳ.ሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ሳ.$ሜ^2$ ይሆናል ?

   ሀ) 84　　ለ) 36

   ሐ) 18　　መ) 80

4. የአንድ የካሬ ቅርጽ ያለው ካፍቴሪያ ስፋቱ 36 $ሜ^2$ ቢሆን የጎኑ ርዝመት ስንት ይሆናል ?

   ሀ) 5 ሜ　　ለ) 6 ሜ

   ሐ) 9 ሜ　　መ) 8 ሜ

5. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠለል ምስል ስፋት 45 ሳ.$ሜ^2$ እና ወርዱ 9 ሳ.ሜ ቢሆን ርዝመቱ ስንት ሳንቲ ሜትር ይሆናል ?

   ሀ) 7 ሳ.ሜ　　ለ) 8 ሳ.ሜ

   ሐ) 5 ሳ.ሜ　　መ) 4 ሳ.ሜ

6. የአንድ ካሬ የጎን ርዝመት ዙሪያ ድምር 24 ሳሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል?

   ሀ) 28 ሳ.$ሜ^2$　　ለ) 48 ሳ.$ሜ^2$

   ሐ) 32 ሳ.$ሜ^2$　　መ) 36 ሳ.$ሜ^2$

7. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠለል ምስል ርዝመት 12 ሳ.ሜ ሲሆን ወርዱ ደግሞ ከርዝመቱ በ 5 ሳ.ሜ ያነሰ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል ?

   ሀ) 25 ሳ.$ሜ^2$　　ለ) 72 ሳ.$ሜ^2$　　ሐ) 45 ሳ.$ሜ^2$　　መ) 60 ሳ.$ሜ^2$

LIVEWORKSHEETS

8. የአንድ ሬክታንግል ርዝመት 6 ሳ.ሜ ወርዱ ደግሞ 4 ሳ.ሜ ነው ፡፡ ሌላ ርዝመቱ ከመጀመሪያው ሬክታንግል በ 2 ሳ.ሜ የሚበልጥ ሬክታንግል ስፋቱ ከመጀመሪያው ሬክታንግል ጋር እኩል እንዲሆን ወርዱ ስንት መሆን አለበት ?

ሀ) 3 ሳ.ሜ　　ለ) 4 ሳ.ሜ

ሐ) 6　　መ) 5

9. ርዝመቱ 24 እና ወርዱ ደግሞ 8 ሳ.ሜ የሆነን ክፍል ርዝመቱ 2 ሳ.ሜ ባለው ስኩዌር ሸክላ ለማንጠፍ ምን ያህል ሸክላዎች ያስፈልጉናል ?

ሀ) 60　　ለ) 42

ሐ) 48　　መ) 52

10. ወርዱ 6 ሳ.ሜ የሆነ ስኩዌር እና ርዝመቱ 4 ሳ.ሜ የሆነ ሬክታንግል እኩል ስፋት እንዲኖራቸው የሬክታንግሉ ወርድ ስንት መሆን አለበት ?

ሀ) 7 ሳ.ሜ　　ለ) 8 ሳ.ሜ

ሐ) 6 ሳ.ሜ　　መ) 9 ሳ.ሜ

11. የአንድ ስኩዌር ርዝመት 5 ሳ.ሜ ነው ፡፡ ርዝመቱ እጥፍ ሲሆን የምናገኘው ስፋት መጠን ከመጀመሪያው ስፋት በምን ያህል ይበልጣል ?


ሀ) 60 ሳ.$ሜ^2$　　ለ) 75 ሳ.$ሜ^2$

ሐ) 25 ሳ.$ሜ^2$　　መ) 35 ሳ.$ሜ^2$

12. በአንድ ርዝመቱ 25 ሜ እና ወርዱ 12 ሜትር በሆነ መሬት ላይ ርዝመቱ 9 ሜትር የሆነ የስኩዌር ቅርጽ ያለው ቤት ተገንብቷል ፡ ፡ ቤቱ ያላረፈበት ክፍት ፎታ ስፋት ምን ያህል ነው ?

ሀ) 300 ሳ.$ሜ^2$　　ለ) 250 ሳ.$ሜ^2$

ሐ) 219 ሳ.$ሜ^2$　　መ) 225ሳ.$ሜ^2$




LIVEWORKSHEETS

13. ዙሪያው 20 ሜ የሆነ ካሬ ክፍል ስፋቱ ምን ያህል ነው ?

ሀ) 12 ሜ$^2$ ለ) 20 ሜ$^2$

ሐ) 25 ሜ$^2$ መ) 16 ሜ$^2$

14. የአንድ ርዝመቱ 7 ሜትር ወርዱ ደግሞ 4 ሜትር ሬክታንግል ቅርጽ ያለው ጠረጴዛ ዙሪያው ስንት ሜትር ይሆናል ?


ሀ) 25 ሜ ለ) 49 ሜ

ሐ) 28 ሜ መ) 22 ሜ

15. ከታች የተመለከተው ምስል ላይ አንድ ርዝመቱ 9 ሳ.ሜ፣ ወርዱ ደግሞ 6 ሳ.ሜ የሆነ ሬክታንግል እና አራት እኩል ቦታ የተከፋፈለ ርዝመቱ 2 ሳ.ሜ የሆነ ስኩዌር ይታያሉ፡፡ ከምስሉ ላይ በቀይ የተቀለመው ክፍል ስፋት ምን ያህል ነው ?

ሀ) 54 ሳ.ሜ$^2$ ለ) 56 ሳ.ሜ$^2$

ሐ) 53 ሳ.ሜ$^2$ መ) 50 ሳ.ሜ$^2$




LIVEWORKSHEETS